በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ታሕሳስ 22 ቀን 2016ዓ.ም

የሰ/መ/ቁ. 248354

**ዳኞች፡-**

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ዋዚሞ ዋሲራ

ሠናይት አድነው

**አመልካች፡-** ቤ.አ.ኤካ ጠቅላላ ንግድ ሥራ ኃ/የተ/የግ/ማ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ሰዓድ ሀሰን ዓሊ

2. አቶ አስክንድር አብዶ መሐመድ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሰኔ 01 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 212245 በመጋቢት 08 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 294375 በግንቦት 21 ቀን 2015 ዓ.ም ያጸናው በመሆኑ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የሥራ ስንብትን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን በስር ፍ/ቤት አመልካች ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሾች ነበሩ፡፡

ተጠሪዎች በሕዳር 29 ቀን 2015 ዓ.ም ያቀረቡት ክስ ይዘት 1ኛ ተጠሪ በወር ደመወዝ 57,758.62(ሃምሳ ሰባት ሺ ሰባት መቶ ሃምሳ ስምንት ከ62/100 ሳ.) እየተከፈላቸው የሽያጭ ዋና

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ክፍል እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ በየወሩ ብር 35,000.00(ሰላሳ አምስት ሺ ) እየተከፈላቸው የገበያና ሽያጭ መምሪያ ስር የገበያ ጥናት እና ልማት ዋና ክፍል ሃላፊ በመሆን ሲሰሩ እንደነበር፤ አመልካች ያለምንም ጥፋት ከህዳር 6 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውላቸውን ያቋረጠ በመሆኑ ስንብቱ ከህግ ውጭ ነው ተብሎ እንዲወሰን እና ከህገወጥ ስንብቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ክፍያዎች እንዲከፈለን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ለቀረበበት ክስ በታህሳስ 11 ቀን 2015 ዓ.ም ዓ.ም በተጻፈ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬነገር መልስ ያቀረበ ሲሆን በመልሱ ተጠሪዎች የተሰናበቱት የማዕድን ሚኒስቴር በሚሊኒየም አዳራሽ ባዘጋጀው ኤግዚቢሽን ላይ የአመልካች ድርጅት የሚያመርታቸውን ምርቶች ለማስተዋወቅና ከደንበኞች ጋር ለማገናኘት የተያዘውን ፕሮግራም በሃላፊነት በመምራት ላይ እያሉ የድርጅቱ ማርብል ማምረቻ ቦታ የሚገኝበትን ቡለን ወረዳ በቤኒሻንጉል ክልል ሆኖ ሳለ ለጎብኚዎች እንዲተዋወቅ በቀረበው የምርቱ ናሙና ላይ የለጠፉት ማስታወሻ ላይ ግን አማራ ክልል ውስጥ የሚገኝ እንደሆነ አድርገው ያልተገባ መልዕክት ለጎብኚዎች ማስተላለፋቸውን፤ ይህም ተግባራቸው ድርጅቱን ከመንግስት፣ከክልሎች፣ ከማህበረሰቡና ከንግድ ሸሪኮች ጋር የማጋጨት አደጋ ውስጥ እንደጣሉት፤ይህም ተጠሪዎች የተሰጣቸውን የስራ ሃላፊነት በከባድ ቸልተኝነት ባለመወጣታቸው በማህበራዊ ሚዲያ በመሰራጨቱ ድርጅቱን ለከባድ እምነት ማጣት፣የስም ማጥፋትና የሞራል ኪሳራ ላይ እንዲወድቅ ያደረጉ በመሆኑ ጥፋቱም ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት በመሆኑ ምክንያት እንዳሰናበታቸው፤ ስለሆነም የተወሰደው እርምጃም በሕግ አግባብ በመሆኑ እና ተጠሪዎች ያገለገሉት ከአንድ ዓመት ያነሰ በመሆኑ የስንብትም ሆነ ካሳ እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የመጠየቅ መብት የላቸውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከተመለከተ በኋላ ለአመልካቾች የተሰጠ የስራ መዘርዝር እንደሌለ እንዲሁም ለኤግዚብሽኑ ዓላማ የምርት አይነት እና አድራሻ መግለጫ ለይቶ የማሳተም እንዲሁም በምርቶች ላይ የመለጠፍ የስራ ሃላፊነት በጽሁፍም ሆነ በቃል በግልጽ ለተጠሪዎች አመልካች እንደሰጠ በማስረጃ እንዳላረጋገጠ፤ በዚህ ምክንያት ቸልተኝነት ወይም ከባድ ቸልተኝነት አለ ለማለት የማያስችል መሆኑን፤ ሃላፊነት ተሰጥቶዋቸዋል ቢባል እንኳን ተጠሪዎች ከሌሎች ሰራተኞች ጋር በመሆን በኤግዚብሽኑ ያለው ምርት ማሳያ ትእይንት በአግባቡ እንዲከናወን በማድረግ ሂደት የተፈጠረን የወረዳ ስም አጻጻፍ ስህተት እንዲታረም ሲያደርጉ እንደነበር፤ ይህን ሲያደርጉ የክልል ስም ስህተት እንዲታረም አለማድረጋቸው ደግሞ ብቻውን ተራ ቸልተኝነት ከሚባል በቀር በግዴለሽነት፣ ስለስራው ሳይጠነቀቁ፣ ውጤቱን ባለማሰብ በከባድ ቸልተኛነት የፈጸሙት ጥፋት ነው ሊባል የሚችል አለመሆኑን፣ አመልካች ደረሰ በሚል ያቀረበውን ጉዳት በተመለከተ በገንዘብ ተምኖ በማስረጃ በማስደገፍ አለማቅረቡን፣ የምርት መግለጫ ላይ በተፈጸመ ግድፈት ምክንያት ተቃውሞ በማስነሳቱ ፋብሪካው ስራ ሳይሰራ ለቀናት ተዘግቷል ቢባልም ከተፈጠረው ግድፈት ጋር ቀጥተኛ የሆነ የምክንያትና ውጤት ግንኙነት እንደሌለው፤ ተጠሪዎች ፈጸሙ የተባለው ድርጊት በራሱ ጉዳት ያላደረሰና በ3ኛ ወገን ህገወጥ ተግባር የደረሰ ጉዳት በመሆኑ አመልካች የወሰደው የስራ ስንብት ሕገወጥ ነው በማለት ከሕገ ወጥ ስንብቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ክፍያዎች አመልካች እንዲከፍል ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች በዚህ ውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ሰኔ 01 ቀን 2015 ዓ.ም የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም ይህን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን ይዘቱም የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች የተመደቡት የሥራ መደብ የስራ መሪ ሆኖ እያለ አይደለም በማለት የሰጡት ውሣኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 42901 በቀን 21/11/2008ዓ.ም በተደጋጋሚ የሰጣቸውን አስገዳጅ ውሣኔዎች የጣሰ መሆኑን፣ ተጠሪዎች በአመልካች ተሰጥቷቸው የነበረውን የሥራ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ አለመወጣታቸውን በስራቸውም ላይ ከባድ ቸልተኝነት ያሳዩ መሆኑን በግልፅ ፍርድ ቤቱ አረጋግጦ እያለ ወይም ደግሞ ጥፋት የለባቸውም ሳይሉ ጥፋተኞች የተባልነው በማይመለከተን ሥራ ነው የሚል የሽሽት ክርክር አቅርበው እያለ ጥፋት ፈጽመዋል ሲሉ በግልጽ ውሣኔ አለመስጠታቸው፣ተጠሪዎች በሥራ ላይ የፈፀሙት ጥፋትና ይህም የፈጠረውን የማኅበራዊ ብጥብጥ አለመረጋጋት እንዲሁም የሥራ መስተጓጎል፣ በአመልካች መልካም ስምና ዝና ላይ ያስከተለውን ጉዳትና የድርጅቱን ሥራ ሊያዘጋ በተቃረበ ሁኔታ ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ለተከናወነ የስም ማጥፋት ዘመቻ ማስፈራሪያዎች የተጋለጠበትን አደገኛ ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤቶች የተረዱ ቢሆንም በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/1/ ላይ በተገለፀው ድንጋጌ አተረጓጎም በሠራተኛው ጥፋትና በአሰሪው ላይ በደረሰ ጉዳት መካከል ስለሚኖረው የምክንያት ውጤት ግንኙነት ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁጥር 64988፣ 104294 የሰጠውን አስገዳጅ ውሣኔዎች አተረጓጎም የጣሰ እና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ተመርምሮ ተጠሪዎች በኤግዚብሽኑ ላይ የምርቶች ትክክለኛ መገኛ ወረዳና ክልል በአግባቡ መጻፍ ሲገባቸው አዛብተው በመጻፋቸው በአመልካችና በአካባቢው አስተዳደር መካከል ያለውን ግንኙነት ሻክሮ አመልካች ላይ ጉዳት መድረሱ አከራካሪ ባልሆነበት ሁኔታ ተጠሪዎች የፈጸሙት ተራ ቸልተኝነት እንጂ ከባድ ቸልተኝነት አይደለም በሚል ስንብቱ ከህግ ውጭ ነው ተብሎ የተወሰነበትን አግባብነት ለማጥራት በሚል ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎችም ነሐሴ 22 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘትም አመልካች ማስረጃን በተመለከተ ያቀረበው የሰበር ችሎቱ ስልጣን አለመሆኑን፣ የስር ፍርድ ቤት የክርክር ሂደትና ብይን /ውሳኔ ላይ ከተመለከተው ውጭ ባልተገባ መንገደ ትርጓሜ በመስጠት የቀረበ ቅሬታ እንደሆነ፣ እርስ በእርሱ የሚጋጭ ክርክር እንዳቀረበ፣ የስር ፍርድ ቤት ተፈጸመ የተባለውን ድርጊት ተራ ቸልተኝነት ነው ማለቱ አግባብነት እንዳለውና፣ በአጠቃላይ ክርክሩን በአግባቡ ተመልክቶና ማስረጃ ሰምቶ የሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ሊጸና ይገባል የሚል ብለዋል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ የአሰሪና ሰራተኛ የስራ ግንኙነት የሚቋረጠዉ በአሰሪዉ ወይም በሰራተኛዉ አነሳሽነት ወይም በህግ በተደነገገዉ መሰረት ወይም በህብረት ስምምነት ወይም በተዋዋይ ወገኖች በሚደረግ ስምምነት መሰረት ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 እንቀጽ 23/1/ የተደነገገ በመሆኑ ከዚህ ዉጪ የሚደረግ የሥራ ዉል ማቋረጥ ሕገ ወጥ በመሆኑ በሕጉ የተመለከተዉን ሃላፊነት የሚያስከትል መሆኑን ተደንግጓል፡፡

በአዋጅ ቁጥር ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/1/ሸ/ ስር በአሠሪዉ ንብረት ወይም ከድርጅቱ ሥራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለዉ ማናቸዉም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ በአሠሪዉ አነሳሽነት ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ዉል የሚያስቋርጥ ምክንያት እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የሥራ ዉል የሚያስቋርጠዉ በአሠሪዉ ንብረት ላይ ወይም ከአሰሪዉ ሥራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለዉ ማንኛዉም ንብረት ላይ በሠራተኛዉ ጉዳት እንዲደርስ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ሠራተኛዉ ጉዳቱን ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ማድረሱ ሲረጋገጥ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 210873 ጥር 26 ቀን 2014 ዓ.ም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በዚህም መሰረት አሠሪዉ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ሠራተኛዉን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ማሰናበት የሚችለዉ አንደኛ በሠራተኛዉ ድርጊት ምክንያት በድርጅቱ ንብረት ላይ ጉዳት መድረሱ ወይም ለደረሰዉ ጉዳት ምክንያቱ የሠራተኛዉ ድርጊት/አል-ድርጊት መሆኑ ሲሆን፣ሌላው ሠራተኛዉ ለደረሰዉ ጉዳት ምክንያት የሆነዉን ድርጊት/አለ-ድርጊት የፈጸመዉ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ በዚህም መሰረት ምንም እንኳ በድርጅቱ ንብረት ላይ ደረሰ ለተባለዉ ጉዳት ቀጥተኛ ምክንያቱ ሠራተኛዉ መሆኑ ቢረጋገጥም የሠራተኛዉ ድርጊት/አል-ድርጊት ለስንብት ምክንያት የሚሆነዉ ድርጊቱን ሆን ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የፈጸመ መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ይህም የሚያሳየዉ ሠራተኛዉ በድንገት/በአጋጣሚ ወይም በተራ ቸልተኝነት በሚፈጽመዉ ድርጊት/አል-ድርጊት ምክንያት በአሠሪዉ ላይ የሚደርስ ጉዳት ሠራተኛዉን ከስራ ለማሰናበት በቂ ምክንያት የማይሆን መሆኑን ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ የማዕድን ሚኒስቴር በሚሊኒየም አዳራሽ ባዘጋጀው ኤግዚቢሽን ላይ የአመልካች ድርጅት የሚያመርታቸውን ምርቶች ለማስተዋወቅና ከደንበኞች ጋር ለማገናኘት በተያዘውን ፕሮግራም ላይ ተጠሪዎች ፕሮግራሙን በሃለፊነት እንዲመሩ ተመድበው ሳለ የድርጅቱ ማርብል ማምረቻ ቦታ የሚገኘው በቤኒሻንጉል ክልል ቡለን ወረዳ ሆኖ ለጎብኚዎች እንዲተዋወቅ በቀረበው የምርቱ ናሙና ላይ አማራ ክልል ውስጥ የሚገኝ እንደሆነ ተድርጎ የተለጠፈ በመሆኑ ለጎብኚዎች ያልተገባ መልዕክት እንዲተላለፍ የተደረገ ስለሆነ ይህም ማህበራዊ ብጥብጥ አለመረጋጋት፣ የሥራ መስተጓጉል፣ በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ እንዲደርስ እና በአመልካች መልካም ስምና ዝና ላይ ጉዳት እንዲደርስ አድርጋል የሚል ሲሆን የስር ፍርድ ቤት አመልካች የዘረዘራቸዉን ጥፋቶች በተጠሪዎች መፈጸም አለመፈጸሙን እና ፈጽመዋል ቢባል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እንኳን ሆነ ብለው ወይም በከባድ ቸልተኝነት ስለመሆኑ ከአዋጁ አንቀጽ 27(1)(ሸ) አንፃር በቂ ምክንያት መሆን አለመሆናቸዉን በጭብጥነት በመያዝ የግራ ቀኝ ማስረጃዎችን ሰምቷል፡፡ የድርጅቱ ማርብል ማምረቻ ቦታ የሚገኘው በቤኒሻንጉል ክልል ቡለን ወረዳ ሆኖ የወረዳው ስም ሲስተካከል የክልሉ ስም ግን አማራ ክልል ተብሎ የተለጠፈ መሆኑን፣ሆኖም ለኤግዚብሽኑ ዓላማ የምርት አይነት እና አድራሻ መግለጫ ለይቶ የማሳተም እንዲሁም በምርቶች ላይ የመለጠፍ የስራ ሃላፊነት በጽሁፍም ሆነ በቃል በግልጽ ለተጠሪዎች አመልካች የሰጠ ስለመሆኑ በማስረጃ አለመረጋገጡን፣ በእርግጥ ተጠሪዎች ፕሮግራሙን በሃለፊነት እንዲመሩ የተመደቡ ቢሆንም እንኳን የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በቀጥታ ሊፈጽሙት የሚገባ ተግባር የነበረ ስለመሆኑ ያልተመለከተ ከመሆኑም ባሻገር ደርጊቱ የተፈጸመዉ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት መሆኑ ያልተረጋገጠ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪዎችን ከስራ ለማሰናበት በቂ ምክንያት አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ማስረጃዎችን በመመዘንም፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ አመልካች የጠቀሳቸው ጉዳት የደረሱ ቢሆንም እንኳን ለደረሰዉ ጉዳት ምክንያቱ የሠራተኞቹ ቀጥተኛ ድርጊት/አል-ድርጊት አለመሆኑ እንዲሁም ተጠሪዎች ለደረሰዉ ጉዳት ምክንያት ተብሎ የተገለጸ ክልል ስም ስህተት የተፈጸመዉ ሆነ ብለው ወይም በከባድ ቸልተኝነት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ በማለት የወሰነ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ በመሆኑ ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን የማረጋገጥ ስልጣን እንደሌለዉ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3-ሀ) እንዲሁም በፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ከፍ ሲል በተመለከተዉ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ሲደርሱ የፈጸሙት የማስረጃ አቀባበል እና የምዘና መርህ ስህተት ስለመኖሩ የዉሳኔዎቹ ይዘት አያሳይም፡፡ ስለሆነም ይህ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን በመመዘን የደረሱበትን ድምዳሜ በድጋሚ ሊመዝን የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ተጠሪዎችን ያሰናበተዉ በህገ ወጥ መንገድ ነዉ በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናዉ ዉሳኔ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ተወስኗል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 294375 በግንቦት 21 ቀን 2015 ዓ.ም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 212245 በመጋቢት 08 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

## ትእዛዝ

በዚህ መዝገብ ሰኔ 14 ቀን 2015 ዓ.ም በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 23800 የተጀመረው አፈጻጸም እንዲታገድ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል**፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !